## ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

## አለአግባብ ለመመስረት ስለሚሞከረዉ ተለጣፊ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ

**ተለጣፊውን ቅንጅት በጭራሽ አንቀበልም! !**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ነጻነት፣ እኩልነትና ፍትሕ ናፍቆ ለነዚህ መሰረታዊ እሴቶች ደንቃራ ከሆነው የኢህአዴግ መንግስት ጋር የመረረ ትግል በማድረግ ላይ ይገኛል:: ይህ የሕዝብ ትግል ያስበረገገው አገዛዝም ዕድሜውን ለማራዘም የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም:: በቅርቡ የተጠነሰሰውና በመታየት ላይ ያለው አዲሱ ድራማ ቅንጅት የሚባል ተለጣፊ ፓርቲ በራሱ አምሳልና ቁጥጥር የመመሥረት ነው::

ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየተሰራ ያለው ተለጣፊ የመደረት ደባ በዓይነቱ አዲስ አይደለም:: እውነተኛ የሕዝብ መሪዎችን ማየት ፈፅሞ የማይሆንለት የመለስ አገዛዝ ከዚህ ቀደም ኦነግን ለማዳከም ኦሕዴድን፣ ኦብኮን ለማዳከም ሌላ ኦብኮን ፈጥሯል:: የመለስ አገዛዝ ይህን መሰል ተለጣፊ የመፈልፈል ስልቱን ከፖለቲካ ፓርቲዎች ባሻገር በሲቪክ ማኅበራትም ላይ ሲጠቀምበት ቆይቷል:: ለዚህም በኢመማ፣ በኢሠማ፣ በኢነጋማ ወዘተ... ላይ የተፈፀሙትን አሻጥሮች እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል::

የአሁኑን የሐሰተኛ ቅንጅት ፓርቲ ምሥረታ በዓይነቱ ለየት  የሚያደርገው በአዲስ አበባ በሚገኘ ው የአሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ የተጠነሰሰ እና ለተግባራዊነቱም መጠነ ሰፊ ጥረት የሚደረገው በኤምባሲው ቅጥር ግቢ መሆኑ ነው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለሠራተኞቻቸው «ቅንጅት የሚባል ፓርቲ የለም፤ ወደፊትም አይኖርም» ሲሉ የነበሩት የአሜሪካ ጉዳይ አስፈፃሚ ወ/ሮ ቪኪ ሀድልስተን አሁን ደግሞ ከመለስ እና ፓርቲያቸውንና ሕዝባቸውን ከካዱ እንደ አየለ ጫሚሶ ከመሳሰሉት ጋር በማበር ተለጣፊውን ቅንጅት ለመመስረት ደፋ ቀና እያሉ ነው::

**ተለጣፊውን ቅንጅት ለመፍጠር ለምን አስፈለገ?**

የኢህአዴግ መንግስት እና የአሜሪካ ጉዳይ አስፈፃሚ የሕዝብ መሪዎች ከታሰሩ ጊዜ  ጀምሮ ከእውነተኛው ቅንጅት ውሳኔ በተቃራኒ የፓርቲው የአዲስ አበባ ከተማ ተመራጮች የከተማዋን አስተዳደር እንዲረከቡ ሲጥሩ ቆይተዋል:: ተመራጮች ከተማዋን ከተረከቡ የመለስ አገዛዝ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የአዲስ አበባን በተቃዋሚዎች መተዳደር በመጥቀስ ዲሞክራሲያዊ ሂደቱ እንደቀጠለ ለማስመሰል ያስችለዋል:: ይሄን የተገነዘቡ በርካታ የከተማዋ ተመራጮች መስተዳደሩን ላለመረከብ ቁርጠኛ አቋም ወስደዋል:: በመለስ አገዛዝ ደጎንነቶች ተደጋጋሚ

ማዋከብና ማስፈራራት ከአሜሪካ ጉዳይ አስፈፃሚዋም ቁጣና ማባበል ቢደርስባቸውም፤ ተመራጮቹ ለእነዚህ ተፅዕኖዎች ባለመንበርከክ ለሕዝባቸውና ለታሰሩት አመራሮቻቸው ያላቸውን ወገንተኝነት አሳይተዋል። የአሜሪካ ኤምባሲም ጥረት አራት ጊዜ ከሽፏል።

ይህ ተደጋጋሚ ሙከራ ሲከሽፍ ጉዳይ አስፈፃሚዋ ከመለስ አገዛዝ ጋር አብረው ሂደቱ እንዲሳካ ጥረት ሲያደርግ የነበረውን የአየለ ጫሚሶ ቡድን መሳሪያ በማድረግ አሁን ደግሞ ተለጣፊ ቅንጅት በማቋቋም «ያለ ፓርቲያችን ከተማዋን አንረከብም»፣ «በእስር ላይ ያሉ አመራሮቻችን ይፈቱ» ያሉ ፅኑ ተመራጮችን «ይኸው ቅንጅት አለ» እያሉ በማታለል አዲስ አበባን እንዲረከቡ የማድረግ እንቅስቃሴ ጀምረዋል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝም አዲስ አበባን ለዚህ ተለጣፊ ቡድን በማስረከብና የሐሰት ድርድር በመጀመር የዴሞክራሲ ሂደቱ እየቀጠለ መሆኑን ለማሳየት አሰፍስፏል። ይህን ካደረገ በኋላ ቀጣዩ እርምጃ የቅንጅት እውነተኛ መሪዎች በእስር ቤት እንዲማቅቁ ማድረግ እና በአሜሪካ ኮንግረስ የሕግ ማውጣት ሂደት ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ነፃነት፣ ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ሕግ እንዳይፀድቅ ማድረግ ነው።

ለዴሞክራሲ ለፍትሕና ለሰብዓዊ መብት በመቆም የምትታወቀውን አሜሪካ ይወክላሉ የተባሉት ወ/ሮ ሃድልስተን እነዚህን ታላላቅ መርሆዎች ይወክሉ ከሆነ ለምን ከእውነተኛ የሕዝብ ፍላጎት በተፃራሪ ራሳቸውን ያስቀምጣሉ? ሕዝብ ከማይደግፋቸው ተለጣፊዎች ጋር መስራትስ የአሜሪካን ዘለቄታዊ ጥቅም ያስጠብቃልን? ለወቅታዊው የአገራችን ችግርስ መፍትሄ ያስገኛልን? በ1997 ዓ.ም የተካሄደን ምርጫስ በ1998 ዓ.ም የተቋቋመ ፓርቲ «አሸነፈ» ማለትስ ቧልት አይሆንምን?

እውነተኛ የሕዝብ መሪዎችን የማስፈታት እና ለአገራችን ችግር ዘላቂ መፍትሔ የማምጣት ተልዕኳችንን ለመወጣት የሚከተለውን ጥሪ እናቀርባለን።

1. የቅንጅትን ሕጋዊ ሕልውና ማግኘትና የመሪዎችን መፈታት በመናፈቅ በቅን ልቦና ለአየለ ጫሚሶ ቡድን ድጋፍ የሰጡ የቅንጅት የፓርላማ ተመራጮች ሴራው ቅንጅትን የሚያጠፋና አመራሮችን በእስር እንዲቆዩ የሚያደርግ መሆኑን ተገንዝበው ድጋፋቸውን እንዲያቆሙ፤ ይህ እንቅስቃሴ እስር ቤት ባሉ አመራሮች ዘንድ ፍፁም ተቀባይነት የሌለው እና ይህም ለተለጣፊዎቹ በግልፅ በመሪዎቹ በራሳቸው እንደተነገራቸው እንዲገነዘቡ፣

2. የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ተመራጮች በተለጣፊው ቅንጅት ስም መስተዳደሩን ከመረከብ እንዲቆጠቡ፣ ማስፈራራቱ እና ማዋከቡ ቢበረታም በፅናት እንዲታገሉ፣

3. የአሜሪካ ጉዳይ አስፈፃሚም ለኢትዮጵያ ችግር ዘለቄታዊ መፍትሔ የማግኘት ጥረታቸውን በሕዝብ ድጋፍ ካላቸው ከታሰሩት የቅንጅት አመራሮች ጋር እንዲያደርጉ፣

4. በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተለጣፊውን ቅንጅት እንደማይቀበሉ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እንዲገልፁ ጥሪያችን እናስተላልፋለን።

5. በዚህ አጋጣሚም ከፍተኛ ጫናና አፈና እየተደረገበት ቢሆንም ኃላፊነቱን በተቻለ መጠን እየተወጣና አመራር እየሰጠ የሚገኘዉ የቅንጅት ቀሪ የአመራር አካል በእስር ላይ ከሚገኙት መሪዎቻችን እንደዚሁም ከህዝባችን ጋር በመመካከር የትግል ስትራጂውን በማደስ ህዝቡን ለተጠናከረ ትግል ለማስተባበር ዝግጅቱን ማጠናቀቁን እንገልጻለን፡፡ ስለሆነም የህዝብ ተመራጮች፡ የቅንጅት አባላት፡ ደጋፊዎችና በፈተና ጽናትህን ያሳየህዉ ህዝባችን ለተጠነሰሰዉ ሴራ ሳትንበረከኩ በቅርቡ ለሚደረገዉ ወሳኝ የመጨረሻ ጥሪ የስነ ልቦና ዝግጅት እንድታደርጉ  ከወዲሁ እናሳስባለን፡፡

የአቶ መለስ አገዛዝ የትግላችንን የትኩረት አቅጣጫ ሊቀይርና ሊያጠፋው እየጣረ ነው፡፡ አሁን የሁላችንም ተልዕኮ መሆን ያለበት መሪዎቻችንን ማስፈታት እና የሕዝብ መንፈስ የሆነውን ቅንጅትን ማዳን ነው፡፡ ተለጣፊው ቅንጅት የመለስ ሴራ መሆኑን ተገንዝበን ሳናወላውል ልናከሽፈው ይገባል፡፡

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ! !**
**ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ**
**አዲስ አበባ፡ ሚያዚያ 6 ቀን 1998 ዓ.ም**